# <u>ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ የመጨረሻዋን የልማት ተራራ እየወጧት ወይስ እየተንከባለሉ ወደታች እየወረዱ!!</u>

በዘንድሮ ወርሃ የካቲት 11/ 2004 ዓ.ም 37ኛው ህወሃት የተመሰረተበትን የልደት በዓል ምክንያት በማድረግ በ63 የመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ 12 የኤፈርት ድርጅቶችና በ8 የግል ባለሃብቶች በድምሩ 83 ድርጅቶች በ70 ገፅ የያዘ ቁጥር 39 2004 ዓ.ም በወይን መፅሔት አዘጋጆች ለጥቅላይ ሚኒስትሩ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ስላለፈው ጊዜ የትግል ጉዞና መጭው ጊዜ ምን አይነት ብሩህ ተስፋ ወይስ ጨለምተኛ የሚል ሰፊ ትንተና አድርገዋል::

— በዚህ ቃለ መጠይቅ ያስቀመጡት መፈክር

ሀ. <u>በትግርኛ</u>

እታ ናይ መጨረሻ ዓቀብ ጥራህ ተሪፋትና ስለዘላ ከምቲ ልሙድ ከምሓድሽ ናይቃልሲ ወነ ተረባሪብና መሊእና ክንሰግራ አለና ይብሉ::

ለ. <u>በአማርኛ ሲተረጎም</u>

እቺ የመጨረሻ ተራራ ብቻ ስለቀረችን እንደተለመደው በአዲስ የትግል ወኔ በመረባረብ በሙሉ ወኔ እንሻገረዋለን ብለዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ምንም እንኳ አንድ አንድ ነጥብ አገራዊ መግለጫ የሚመስል ቢሆንም አብዛኛው አጀንዳቸው የትግራይን ክልል የወደፊት ተስፋ ምን ሊሆን እንደሚችል ያጠነጠነ፣ ተጨባጭነት የጎደለውና ለትግራይ ህዝብ የህልም እንጀራ የሚያበላ ነበር::

ለ39ኛ ግዜ ታትሞ የወጣው መፅሔት ባለ 70 ገፅ 83 ድርጅቶች እጅግ ብዙ የመንግስት፣ የኤፈርት፣ የጥረትና የግል ባለሃብቶች እጅግ በብዙ ገንዘብ እስፖንሰር ያደረጉለት መፅሔት ነው:: ይህ መፅሔት ለመታተም የተዋጣው ገንዘብ ብዛት በመቶ ሺ ወይም በሚሊዮን ብር ይቆጠራል የሚል ጥያቄ ቢመጣ ትዝብቱን ለአንባብያን ልተወው:: አንድ ነገር ግን ጠቁሜ ልለፍ:: ወይን መፅሔት፣ ወይን ጋዜጣና ድምፅ ወያኔ የህወሃት ልሳኖች ናቸው:: እነዚህ ልሳኖች ለመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ የፌዴራልና የክልል ቢሮዎች ባለስልጣን መስሪያ ቤቶችና የወረዳ አስተዳደሮችን ማስታወቅያ በመስራት ብዙ ገንዘብ ገቢ ያደርጉ እንደነበሩ የሚታወቅ ነው:: በማስታወቂያ ምክንያት እየተደረገ ገንዘብ ከመሰብሰብ አልፎ ባለፉው ዓመታት ለወይን ጋዜጣና መፅሔት ማተሚያና ፅህፈት ቤት ግዙፍ ህንፃ ለማሰራት ለትግራይ ክልል ቢሮዎችና ፅህፈት ቤቶች፣ ለመንግስት ሰራተኞች፣ ለነጋዴዎችና የገጠር ገበሬዎች ከሚያገኟት ገንዘብ በካድሬዎች እየተተመነላቸው ብዙ ገንዘብ ተሰብስቧል::

እዚህ ላይ አንደኛ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙሃን መገናኛ ማስታወቂያ እየሰሩ ገንዘብ ሊሰበስቡ ይቅርና በህገ መንግስቱ መሰረት ሬድዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ሊከፍቱ አይችሉም የሚል ህግ በግልፅ ተቀምጧል:: ህገ መንግስቱ ግን ለህወሃት ኢህአዴግና አጋሮቹ የንግድ ድርጅቶች እንዳይመሰርቱ የሚያግዳቸው ህግ የለም ብሎም ለመናገር እርግጠኛች ነን:: ለዚሁ ማረጋገጫ በህወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ የሚመሩ የሚተዳደሩና ገቢያቸውም ማንም የማያውቀው ግን ደግሞ የትግራይ ህዝብ ንብረት ነው ተብሎ የሚሸቀጥለት በብዙ ቢልዮን ብር የሚቆጠር ካፒታል ያላቸው፣ በበአዴን ንብረትነት የሚታወቁ እነዚህም በቢልዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚገመት ጥረት የሚባል የንግድ ድርጅት እንዲሁም ሃብታቸው እንደ ኤፈርትና ጥረት ባይሆንም የኦሮሞ ድርጅት ኦህዴድና የደቡብ ህዝቦች ድርጅት አብዛኞች በባለንብረትነት የሚያዟቸው ሃብት አላቸው::

የህወሃት ኢህአዴግ መንግስት ራሱ በህዝብ ትግልና መስዋዕትነት ተረቅቆ ፀድቆ የተመሰረተውን ህገ መንግስት ራሱ እየናደ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የህወሃት ኢህአዴግ ተወዳዳሪ ሆነው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ለሚያካሂዱ ፓርቲዎች ይቅርና በንግድ ሊሰማሩም ሆነ የሬድዮ ጣቢያ ሊመሰርቱ ፓርቲዎቹ ከህዝብ የገንዘብ ድጋፍ እንዳያገኙ ያልነበረ ህግ በማውጣት ተወዳዳሪ ፓርቲዎች በኢኮኖሚ ችግር ቀጭጨው እንዲከስሙ እያደረገ ነው:: ስለሆነም በስልጣን ያለው ህወሃት ኢህአዴግ ያለውን የአገራችንን ህገ መንግስት እየናደ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ ምክንያት እየፈጠረ እያሚጠጠ ለፓርቲው ጥቅም እያዋለው እንዳለ 39ኛው ወይን መፅሔት እንደ ማስረጃነት የሚታይ ነው:: የወይን መፅሔት ስፖንሰር የሆኑት ድርጅቶች በዚህ ፅሁፍ በስተመጨረሻ ይመልከቱ::

ከዚህ በመቀጠል የጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ቃለ መጠይቅ አንኳር አንኳሩን ለመተቸት እሞክራለሁ::

<u>ወይንና ጥያቄው፦</u> በትግራይ እየተሰሩ የቆዩና አሁንም በመሰራት የሚገኙ የልማት ስራዎች የህዝቡን ኑሮ በመለወጥ የደረሰበት ደረጃ ምን ይመስላል?

ጠ/ ሚኒስትር መለስ እርዳታ የሚያስፈልገው ህዝብ እየቀነሰ መጥቷል የህዝቡም ኑሮ ተሻሽሏል ይሉናል::

እኔ እንደሚመስለኝ ጠ/ ሚኒስትር መለስ በትግራይ ህዝብ ያለው ረሃብ ስደትና ጥልቀት ያለው ድህነት መኖሩን አለማወቃቸው ነው? እየሸወዱን ነው ወይስ በትግራይ ያለው መዋቅራቸው ሃቅ ያልሆነ ሪፖርት እየሰጣቸው ነው?

በቅርብ ግዜ የትግራይ መሪዎች 800,000 በሴፍቲኔት ተረጂዎች ነበሩን ብለዋል:: እነዚህ በሴፍቲኔት ተረጅዎች ሃብታም ሆነው ተመርቀዋል ሲባል ሰምተናል:: ሌላው በአሁኑ ግዜ ወደ ጅቡቲና ሱዳን የሚፈልሰው ወጣት ስንት ነው:: ሰርተው ለመብላት የስራ መስክ አጥተው በከተማ ሆነ በገጠር የሚያደርጉትን አጥተው በቤተሰቦቻቸው ጫንቃ ተጭነው በድህነት አለንጋ እየተገረፉ የሚገኙት ስንት ናቸው:: የትግራይ ገጠሮችና ከተሞች ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የራቁ አልነበሩም:: በወረቀት ሰንጠረዥ በፐርሰንት ተሞልቶ በማንበብ ጊዜዎን ከሚያሳልፉ በየአካባቢው እንደ ናሙና ቀበሌዎችን በመምረጥ ድንገተኛ ገበሬው ወጣቱን ምሁሩን ቢጠይቁስ:: ምክንያቱም በትግራይ ክልል ያለ መዋቅርዎ ስለማይሰራ ሁሉ ህዝብ ስለሚያውቅ ነው:: በአሁኑ ግዜ እኮ ከትግራይ ክልል ወረዳዎች የአርሶ አደር ምርት ወደ ከተማ ገብቶ የሚሸጥ ምርጥ የለም:: እህል፣ ቲማቲም፣ ሽንኩርት፣ በርበሬ የመሳሰሉት እኮ ከደሴ፣ ከጎጃም፣ ከሸዋ ነው የሚመጣው ያለው:: ዋጋውም ደግሞ ከ1000 — 1400 ብር ጤፍ ይሸመታል:: የወጥ እህል አይቀመስም:: የትግራይ ገጠር ህዝብ እኮ ያቺ የነበረች እኔና እርስዎ የምናውቃትን አቡጀዲ አልቀየረም:: አንድ አንድ ሰልባጅ ቢለብሱም እድሜ ያላት አይደለችም እሷም ብትሆን ውድ ሆናለች:: ለመሆኑ የትግራይ ህዝብ ተመችቶታል ብለው ሲናገሩ የምቸቱ መለኪያዎ ምንድነው?

ሌላው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ምንም እንኳ በሚፈለገው ሁኔታ ባይጓዝም ባለፈው አንድ ዓመት ተኩል ትንሽ ለውጦችና መሻሻል አሳይተዋል ብለዋል::

አሁንም ጠ/ ሚኒስትር መለስ የሚሉት ተጨባጭነት የለውም:: ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ከ2002 የምርጫ ዋዜማ የዩኒቨርስቲ ምሩቃኖች ያቀፈ 800 ማህበራት ተቋቁመው ነበር:: ከምርጫ በኋላ 100% ፈርሰው ጠፍተዋል:: ድሮውንም ለጊዜያዊ ማስታገሻ ነበር የተደራጀው::

ሌሎች መቀሌን እንደሞዴል በመውሰድ እስከ 1400 ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ነበሩ:: በአሁኑ ጊዜ የመቀሌ ከተማ ባለስልጣኖች፣ የክልሉ ከተማ ልማትና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሃላፊና

የክልሉ ምክትል ፕሬዚዳንት በየነ መክሩ ያረጋገጡት ሁሉም ማህበራት ከስረው በአሁኑ ግዜ እንደገና በአክስዮን ማህበር በቫት እየተመዘገቡ በመያዣ ከባንክ እየተበደሩ እንዲሰሩ ማደራጀት ተጀምሯል:: ውጤቱን አብረን እንየው:: በዚህም ጠ/ ሚኒስትሩ በቂ ሪፖርት የላቸውም:: ይቅርና በወረዳና ዞኖች መቀሌን የሚያህል ትልቅ ከተማ የነበሩ ማህበራት ፍፁም ከስመዋል:: እንደገና ያጥኑት ደጋግመው መዋቅርዎን ይፈትሹ:: ምን ሰራህ? የት ትውላለህ ታድራለህ? ይበሉት:: የደህንነት መዋቅርዎ ለሰላማዊ ተወዳዳሪ ፓርቲዎችን ከማሳደድ ለነዚያ የእርስዎ መዋቅር እርስዎ ያመኑዋቸው የመንግስት ሰራተኞች ሌቦች ናቸው:: እንዳሉት የጊዜ የገንዘብና ንብረት ሙሰኞችና ሌቦችን ቢከታተሉ ለአገር፣ ለህዝብና ለስልጣኖት መራዘም ጠቃሚ ነበር:: ጠቅላይ ሚኒስትር በአሁኑ ግዜ እኮ የትግራይ ክልል ለህብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጠ አይደለም ያሉት:: እርስዎም ይህ ጠፍቶቦት አይመስለኝም::

በአሁኑ ግዜ ልመናና ተረጂነትን (ተመፅዋችነትን) ለመሻር በምንችልበት ደረጃ እንገኛለን ብለዋል::

ምን ይዘው ምን ተዓምር የሚሰራ ሃይል መጣና አሁን ያሉት ድህነትን ተመፅዋችነትን የሚቀርፍ ምን አይነት ብዙ ሰራተኛ የሚያቅፍ ነገር ተፈጠረ:: በትግራይ የኤፈርት ካልሆኑ ብዙ ሰራተኛ ሊያቅፍ የሚችሉ ፋብሪካዎች የት አሉ? የኤፈርት ፋብሪካዎችም በዘመድ አዝማድ ተሳስረው የሚሰሩ ከ30,000 በላይ ሰራተኛ መች ይሸከማሉና? ባለፈው ዓመታት በትግራይ ይህን ያህል ቢልዮን ንብረት ያላቸው ኢንቨስተሮች ገብተዋልና እነዚህ ስራ ሲጀምሩ 60 ሺ ወይም 80 ሺ ከዚያም በላይ ስራ ይፈጥራሉ ይባል ነበር:: በተጨባጭ አሁን የት አለ? በ10 ሺዎች የሚቆጠሩ ባለሙያና ሙያ የሌላቸው ሰራተኞች ትላንት የነበሩ ህንፃ ተቋራጮች እኮ አሁን የሉም:: ወደ አዲስ አበባ፣ ክልሎችና ወደ ደቢብ ሱዳን(ጁባ) ገብተዋል:: በገጠር እርስዎ እንደሚያውቁት ከ1994 ዓ.ም በኋላ መሬት አልተሸነሸነም፤ ቢሸነሸንም ምንም አትዳረስም:: ዋናው መፍትሔ የነበረው መሬት ለሌለው ሌላ ስራ መፍጠር ነበር ግን አልተቻለም:: በአሁኑ ግዜ በትግራይ የገጠር ህዝብ ከ40 ዓመት ዕድሜ በታች ጉንቻውን የሚያሳርፍበት የስራ መስክ የለም:: ይህ ሃይል ዋና አምራች ከመሆኑ አልፎ ከጠቅላላው ህዝብ በቆጠራ የተረጋገጠ ማረጋገጫ እንኳን ባይኖረንም እጅግ ከፍተኛ ፐርሰንት መሆኑ ግን እርስዎም ያውቃሉ:: ታድያ ይህ ጉልበት መሄን እያለ ድህነቱን እንዴት ልንቀርፈው ተቃርበናል ይሉናል::

በከተሞች ስራ አጥ እጅጉን ብዙ ነው:: ደግሞም የተማረ ሰው በገጠርም ያለ ወጣት አብዛኛው ቀለም የቆጠረ ነው:: እዚህም የሰጡን መልስ ለእኔም ለህዝቡም አላረካንም::

<u>ወይን፦</u> ኢኮኖሚያዊ እድገት በሃገር ደረጃ በየዓመቱ የሁለት ዲጂት እርምጃ አለ እያሳየንም ቆይቷል:: በዚህ መሰረት ይህ የእድገት ውጤት የሚገለፅበት የስራ መስክ የትኛው ነው?

የጠ/ ሚ/ መለስ መልስ በአሁኑ ግዜ በከተማ ልማት የተሰማራ የልማት ሃይል ሰው አለ:: በተጨማሪ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በኢንዱስትሪም በምዕራብ ትግራይ የሚሰራ ያለው የስኳር ፋብሪካ አለ:: በሃገር ደረጃም 10 የስኳር ፋብሪካዎች አሉን:: የባለሃብት ኢንቨስትመንትም አለ:: በዋናነት ደግሞ በገጠር እርሻ በከተሞች ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በማሰራት ለውጥ እየመጣ ነው ብለውናል::

አሁንም ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ከስመዋል:: በከተማ ልማት የሚባለው ምናልባት አዲስ አበባ እየተሰራ ነው ቶሎ ቶሎም ቤቱ ይሸጣል:: በትግራይ ግን ኮንደሚንየም ከተጀመረ ዓመታት ቢያስቆጥርም አብዛኛው አላለቀም:: በጊዜ ርዝመትና ሙስና ከ3 ግዜ በላይ በጀቱ ተበልቷል:: ስለዚህ ከተማ ልማት ትግራይ ይቅርና ስራ ፈጥሮ ድህነትን ሊያጠፋ ለራሱም መኖሩ ያጠራጥራል:: የቤቶች ኤጀንሲ በሙስና ሲታሰር ሲፈታ ነው የነበረው ሙሰኞች ግን ሲፈረድባቸው አላየንም::

በምዕራብ ትግራይ ስኳር ፋብሪካ አለን የሚባለውም በረጅም ግዜ አንፃር ጠቃሚ ነው:: ከ20 እስከ 30 ሺ ሰራተኛ ከዚያ በላይም ሊይዝ ይችላል ለመቼ ነው:: የስኳር ኢንዱስትሪዎችም በ2 ወይም 3 ዓመታት ይደርሳል ተብሎ ነበር:: አሁን ግን የፋይናንስ ችግር አለ እየተባለ ነው:: ስለዚህ ስኳር ፋብሪካውም ግን ገና ለወደፊቱ ነው:: አሁን ስራ አጡ ምን በልቶ ይደር?

ሌላው በከተማ ልማት ያለው ችግር የነባር ይዞታ የሊዝ አዋጅ ካመጡ ጀምሮ የኮንስትራክሽን ስራ አቁመዋል:: ስለዚህ ስራ አጥነትና ድህነት እየተባባሰበት ነው:: ጠ/ ሚኒስቴር አሁንም የኢንፎርሜሽን ምንጭዎን ይፈትሹ:: ግን እንዴት አድርገው ይፈትሹ መዋቅርዎ ላሽቋልና::

እንደዚሁ ጠ/ ሚኒስትሩ ያሉት በምዕራብ ትግራይ 250 ሺ ሄክታር ስኳር እንዘራለን ይህ ደግሞ ያለጥርጥር ድልን እናገኛለን ይላሉ::

በኔ በኩል አሁን የስኳር ስትራቴጂ በተራዘመ ግዜ ጥሩ ነው አሁን ያለው ችግር በምን ይገታ መልስዎ ለማንም አላረካም::

ጠ/ ሚኒስትሩ ሲሉ በልማት ሃይሎች አይን ሲታይ በገጠር እጅጉን የሚያበረታታ ሁኔታ እየታየ ነው:: ይህ ደግሞ ገበሬውን በተለይ በትግራይ ህዝቡን ከጫፍ እስከ ጫፍ አደራጅተህ በተፈጥሮ ሃብትና በውሃ በማሳተፍ ብዙ ስራ ሊሰራ ይችላል ድህነትም ይጠፋል ይላሉ::

ህዝብ በማደራጀት የማይሰራ ነገር የለም:: የትግራይ ህዝብ ጥሩ መሪ ከሁሉም ከመስረቅና ጊዜ ከማጥፋት ወዘተ የፀዳ ከሆነ ታሪክ ይሰራል:: በትግሉ ወቅት ሲራብ ተርበን ሲቸግረው ተቸግረን እየመራነው ጉልበቱስ ይቅር ልጆቹን ሽልሞና አልብሶ ወደ ጦርነት አውድማ ይከተው ነበር:: ራሱንም ወደ እሳት ይማግድ ነበር:: አሁን ግን መሪ የሚባል ከቀበሌ እስከ ክልል አልፎም እስከ ፌዴራል ባለስልጣኖች አመጋገባቸው፣ ህክምናቸውና አለባበሳቸው ተቀይሮ ፊታቸው እንኮይና ብርቱካን መስሎ ልጆቻቸው በአገር ውስጥ ምርጥ ት/ቤት ሲማሩ ከዚያም አልፎ በቻይና፣ በአሜሪካ፣ በእንግሊዝና ጃፓን ሲሄዱ ሲያይ የዕለት ኑሮዋቸው ፍፁም ከህብረተሰቡ የተወለዱ የማይመስሉ መሪዎች እያሉ ህዝቡ እንዴት ብሎ ነው የሚያምናችሁ::

ሌላው ተፈጥሮ ይጠበቅ ከተባለ ዓመታት አስቆጥሮዋል:: ትግራይም በሃገር ደረጃ ሞዴል ናት እየተባለ እንሰማለን:: ተራራዎቹም በእፅዋት ተሸፍነዋል ያሉንን እስቲ ሃቁን እንነጋገር:: በትግራይ ክልል በውቅሮና አካባቢዋ እንደ አብርሃ ወአፅብሃ (ሚሊኒየም ቪሌጅ) በአድዋና በሽሬ ደጋማ ተራሮች ጥበቃ ተደርጎላቸው እጅጉን ለምተዋል:: እነዚህ ተራሮች ከትግራይ የቆዳ ስፋት ስንት ፐርሰንት ይሆናል:: እጅግ እጅግ አነስተኛ ነው::

እስቲ እኔና እርስዎ የምናውቀው ከማይጨው ሁመራ ጥርጊያ ይዘን ስንጓዝ ከነዚያ የጠቀስኳቸው ተራራዎች ውጭ እፅዋት አለ ወይ? የወርኢ፣ የህርሚ፣ የአገው ምድር፣ በምዕራብ ከሽሬ እስከ ሁመራ፣ ከዋጅራት ሰሓርትን ተንቤን ዓዴትና ዛናን እንመልከት:: እስከ 1983 ዓ.ም ጫካ በቀርከሃና ሌሎች የተሸፈነ ነበር:: አሁን ምን አለ ለአይን የሚያስጠላ ምድረ በዳ ነው:: እስቲ እባክዎ በሄሊኮፕተር ይቅርና ትግራይን መላው ሃገራችንን ለመታዘብ 3 ቀን አይፈጅብዎትም:: የውሸት ሪፖርት ሰምተውና አንብበው መግለጫ ከሚሰጡን በአይንዎ አይተው ቃለ ምስክርነትዎን ቢሰጡ ይሻልዎታል:: አለበለዚያ በወይን መፅሔት የሰጡን የህልም እንጀራ የማይታይ የማይዳሰስ የማይቀመስ ከመሆኑም በላይ ጭራሹን መተማመን አሳጣን::

<u>ጠያቂው ወይን መፅሔት፦</u>

በትግራይ በእርሻና ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት (የደአትን) የልማት ሰራዊት በመፍጠር ለገጠርና የከተማ ዕቅዶች ለማቀላጠፍ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ውጤቱ እንዴት ይመዝኑታል?

ጠ/ ሚኒስትር መለስ፦ ሁኔታው ተስፋ የሚሰጥ ነው::በገጠር ይሁን በከተማ ዘንድሮ የተጀመሩ አሉ:: በአንድ አንድ ወረዳዎች ድክመቶች አሉ:: በአብዛኛው ጥሩ ናቸው:: የእናቶችና ህፃናት ህክምናና እንክብካቤ በጣም ያስደስታል::

ስራ አጥነትን በሚመለከት ዘንድሮ 300,000 (ሶስት መቶ ሺ) በገጠርና በከተማ አንድ አይነት ስራ ሊያገኝ ነው የሚል መረጃ ነው ያለኝ:: ይህ 300,000 ሰራተኛ ጉልበቱ ተራራዎችን የሚያፈርስ ነው ይሉናል::

የኔ አስተያየት በህፃናትና እናቶች ያለው እንክብካቤ የተሟላ እንደሆነ ይነግሩናል:: ጠ/ ሚኒስትር አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ:: በሰሜን ምዕራብ ዞንና አካባቢው ያለው ሰው ጨራሽ በሽታ መንደሮችን ያወደመ ብዙ አዛውንትን፣ ወጣት፣ እናቶችና ህፃናቶችን 12 ዓመት ሙሉ የቀጠፈ መድሓኒት ያልተገኘለት ሰው ገዳይና ዘርን ያጠፋ ጄኖሳይድ በሽታ እናቶችና ህፃናቶችን የገደለ እነዚህን መዋቅርዎ ለምን አልነገርዎትም:: እንዴት ደስ ብሎኛል ብለው ይደመድማሉ::አሁንም ይህችን ሃገር ያለአንድ የመዋቅር ሰንሰለት እየመርዋት እንዳሉ የሚያሳይ አነጋገር ነው እየነገሩን ያሉት:: ክቡር ጠ/ ሚኒስትር ቁርጠኛ ሆነው ለህዝብ የሚያስቡ ከሆነ ያ ለእኔና ለእርስዎ ደብቆ እንዲሁም ለሌሎች የህወሃት መሪዎች ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ ትኩስ ቂጣ ፈትፍቶ ያበላን፣ ወፍራም የዳጉሳ ጠላ ያጠጣን፣ ህዝቡ በቃሬዛ የተሸከመን፣ ልጆቹን ሸኝቶ የሰጠን ህዝብ ሲያልቁ ምንም ትንፍሽ የማይሉ የመንግስት ባለስልጣናት መዋቅር ጄኖሳይድ እንደፈፀሙ ለፍርድ ለምን አይቀርቡም:: ጠ/ ሚኒስትር ለምን በእነዚህ አልጨከኑም:: እዚህ ላይ እርስዎ ስለዚህ በሽታ መረጃ አይኖሮትም የሚል እምነት የለኝም:: አንድ አንድ ጊዜ ለመዋቅርዎ አለመተማመን ነው መሰል አንደኛ ከየዞኑ ወረዳዎች ግለሰቦች እየጠሩ መረጃን ያሰባስባሉ ይባላል:: ሁለተኛ አንድ አንድ ጊዜ በመቀሌ፣ አዲግራት፣ አድዋና አክሱም እየሄዱ ሽሬና ሁመራ እንኳን አልሄዱም በሌሎች ግን በአቋራጭ ያገር ሽማግሌዎች ግለሰቦች አንድ አንድ ግዜም በጭለማ ያናግሩ እንደሆነ ነው የሚታወቅ:: ስለዚህ የጄኖሳይድ በሽታም ከእርስዎ የተሰወረ አይመስለኝም:: ስለሆነም የህፃናትና እናቶች እንክብካቤ አስደስቶኛል ማለትዎ አርቴፊሽያል ደስታ ነው በበኩሌ አልቀበለውም:: ምክንያቱም በትግራይ ያለውን የመድሓኒት ችግርን እያወቁ ሴቶች ምጥ ተይዘው ማደንዘዣ፣ ጎዝ፣ ጓንትና ሌሎች መድሓኒቶች አይደለም የሚሉት ሌላ ቦታ ይቅርና ከፍተኛ የህክምና ማዕከል የዓይደር ሆስፒታልና መቀሌ ሆስፒታልን ይጠይቁ:: ሃኪሞችም እኮ የተሟሉ አይደሉም:: ስለዚህ ለምን ከተጨባጭ መረጃ አይነሱም:: አሁንም ያስደሰትዎት ነገር አርቴፊሽያል ነው::

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ከላይ እንደገለፅኩት በአሁኑ ግዜ ከዓይደር ሆስፒታል ውጭ በትግራይ ከ20 የማይበልጡ ዶክተሮች ነው ያሉት:: እነሱም በአያያዝ መጥፎነት ይሁን በአስተዳደር ችግር ምክንያት ከትግራይ እየለቀቁ የሚሄዱ ብዙ ናቸው:: በትግራይ እኮ ጤና ኬላዎች፣ ጤና ጣቢያዎችና ክሊኒኮች በሽ ናቸው ግን ሃኪምም ሆነ መድሃኒት የለም:: በትክክል ህዝብ ጤናማ እንዲሆን ሰርቶ በልቶ እንዲያድር ከተፈለገ የትግራይ ዓመታዊ በጀት ከማስፈፀም አቅም ማነስ በየዓመቱ ወደ እርስዎ የሚመለስ ገንዘብ በሚልዮኖች የሚቆጠር ነው:: በዘንድሮ ብቻ 930,000,000 (ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሚልዮን ብር) አልተመለሰሎትም:: በዚህ ህዝብን ለማከም ሆነ ስራን ለመፍጠር በቂ ገንዘብ አይደለም ይላሉ:: ይህንንም ይመልከቱ::

ሌላው 300,000 (ሶስት መቶ ሺ) ወጣት ዘንድሮ ወደ ስራ ሊሰማራ ነው ተብለናል ብለዋል:: በበኩሌ አሁንም ይህ መረጃ ከየት እንዴት በመሰለ ሰው ነው የመጣው:: ሶስት መቶ ሺ ሰው በየትኛው ፕሮጀክት ነው የሚሰራው ብለው መጠየቅ ነበረብዎት:: ጠ/ ሚኒስትር እኔ የተወዳዳሪ ፓርቲ አባል ስለሆንኩ አይደለም የምቃወምዎት ያለሁት:: አንደኛ ዜጋ በመሆኔና ሁለተኛው ደግሞ በትግል ላይ ስላለሁኝ ነው:: በገጠር ሆነ በከተማ ያለውን መረጃ እንደማያመልጠኝ እርስዎ ያውቁኛል:: ስለዚህ ይህ ጉዳይ ሊሆን ስለማይችል ነው የምቃወምዎት:: ሶስት መቶ ሺ ሰው ስራ ቢያገኝና አንድ ሰው ሁለት ልጆችና ሚስት ቢኖረው በአጠቃላይ 1.2

ሚልዮን የሰው ፍጡር በልቶ ያድራል ማለት ነው:: ይህ ከሆነማ ልመና የሚባል ነገር ጠፋ ማለት ነው::

እኔ የሚመስለኝ ሁመራ በሰኔ ወር 15—20 ቀን እህል ለመዝራት በአረም ወቅት 30 ቀናት በመኸር ወቅት ደግሞ ለ40 ቀናት በድምሩ 2 ወር በአመት ለስራ ይሰማራል:: ያም ሆኖ 300,000 ሰው ሊሰማራ አይችልም:: ይህን ሃይል ወደ ስራ የሚቀበል ፕሮጀክት ካለዎ ያ ሁሉ ወጣት ወንድና ሴት በሱዳንና ሌሎች አገሮች ለምን ይሰደዳል:: እናም ጠ/ ሚኒስትር አሁንም ያለዎትን መረጃ ይፈትሹት:: እኔ የሚሉት ሁሉ ምኞት ከሆነ እንደ ምኞት ጥሩ ነው:: በተጨባጭ ግን የማይሆንና ስሜታዊ ነው:: ግን ለምንድን ነው በአሁኑ ግዜ በተደጋጋሚ ስሜታዊ የሆኑ መግለጫዎችን ያበዛሉ:: ለህዝብ ያልሆነ የህልም እንጀራ ማብላት ትርፉ መናናቅ ነው የሚሆነው:: ፍቃደኛ ከሆኑ ከምሁራኑ፣ ከሙያተኛው፣ ከነዋሪው ህዝብና ከተወዳዳሪ ፓርቲዎች ጋር ቢመካከሩ ካለው መዋቅርዎ ጋር ብቻ መማከሩ ትርጉም የለውም:: በአሁኑ ግዜ እኮ እንደ ድሮው የትግል ወቅት ይህ ድክመት አለኝ ብሎ የሚያምን መዋቅር የለዎትም:: በቴሌቪዥን መስኮት ወጥተው በክልሉ የሌለው የማይታይ የማይጨበጥ የሚናገሩ ወገኖች እኮ እጅጉን ብዙ ናቸው:: በአሁኑ ግዜ አጋንኖ መናገር ፋሽን ሆኖዋል:: ይህን ሁሉ ህዝብ ያውቀዋል:: እርስዎም ይህንን እየደገፉ ነው ይመስለኛል::

<u>ወይን መፅሔት</u>፦ ኪራይ ሰብሳቢነትን ለመመከት የአደጋው ምንጮችን ለመዝጋት ቀደም ብለው በተለይ ደግሞ ከቅርብ ግዜ ወዲህ እየባሰበት የመጣ እንቅስቃሴ አለ:: ይህ እንቅስቃሴ በየትኛው ደረጃ ይገኛል? ምንስ ውጤት አመጣ ለመባል ይቻላል?

<u>ጠ/ ሚ/ መለስ</u>፦ በአሁኑ ግዜ በትግራይ ከከተማ መሬት የተያያዘ ኪራይ ሰብሳቢነት ቀንሷል:: አሰራሩ በመሻሻሉ ቀደም ብሎ ኪራይ ሰብሳቢነት ነበር:: በአዲስ አበባ ጥቂት ሰዎች ሁሉንም ነገር ይዘውት ነበር:: በአዲስ አበባ መርካቶ ቦምብ ተራ የሚባል ቦታ አለ:: እዚያ ያሉት ነጋዴዎች ናቸው ይህችን ሃገር እያሽከረከሯት ያሉት ይሉናል:: ትግራይ ስንመጣ ግን በነጋዴዎችና በመንግስት የክልሉ አስተዳደር መካከል የመግባባት መንፈስ ስላለ ተወያይተህ የመስራት መንፈስ ተፈጥሯል ይላሉ:: በተለይ ደግሞ ኪራይ ሰብሳቢነት ከምንጩ ለማድረቅ በትግራይ ክልል ተጀምሮ ያለ ስራ ለሃገራችን በሙሉ በምሳሌነት (በሞዴልነት) ይቀመጣል ይላሉ::

አሁንም በትግራይ ያለ ኪራይ ሰብሳቢነት ስር የሰደደና በሃገር ደረጃ ላለው ኪራይ ሰብሳቢነት የተጨማለቀ አስተዳደርና አፈና የነገሰበት ህዝብ ተረጋግቶ ሰርቶ እንዳይኖር ሰግቶ የሚኖርበት ሰው የሚታየውና የሚያውቀውን እንዳይናገር ትግራይ የዝምታ መንደር መሆንዋ ትግራይ ጥቂት የመንግስት ባለስልጣናት ብቻ ናጥጠው የሚኖሩባት ህብረተሰቡ ሰርቶ የማይኖርባት ሁሉም ነገር በሙስና የሚሰራባት ክልል ናት::

ጠ/ ሚኒስትር ለምን የእርስዎ ሃብት የሆነውን የኤፈርት ሃብት የአስተዳደር ጉዳይ ለምን አናይም:: ይህ በ10 ቢልዮን የሚቆጠር ካፒታል ያሉት ትላልቅ ድርጅቶች ማን ያስተዳድረዋል? ገቢና ወጭውስ ይታወቃል ወይ? ትርፉስ የት አለ? በማን እጅ? ግልፅነትና ተጠያቂነትስ አለው ወይ? 20 ዓመት ሙሉ በህዝብ ባለንብረትነት የሚነገርላቸው ግን ደግሞ ህዝቡ ሳንቲም እንኳን ያልቀመሰ የት አለ? የትግራይ ክልል የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ አይደለም ወይ?

እስቲ የመሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ ባለፉት ዓመታት ስንት ሙሰኞችን ነው ያፈራው? ሌሎች የኤፈርት ድርጅቶችስ ስንት ኪራይ ሰብሳቢ ነው የፈበረከው? ታዲያ ስም ይወጣል ከቤት ይቀበላል ጎረቤት እንደሚባለው በትግራይ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ኤፈርትና ህወሃት አይደሉም? በሃገር ደረጃስ የህወሃት ኢህአዴግ ሰዎችና ወገኖቻቸው አይደሉም የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ? አሁን እኮ ጠ/ ሚኒስትር በውስጥዎ ያለው ኪራይ ሰብሳቢነት ሊቆርጡ ከፈለጉ እጅዎና እግርዎትን ሊቆርጡ ካልሆነ በስተቀር ምንም ለመስራት ከማይችሉበት ሁኔታ ነው ያሉት::

በቅርብ ግዜ አቶ ስብሃት ነጋ ኢትዮጵያ በሙስና ከኬንያ ናይጀርያና ከሌሎች ሃገሮች ትሻላለች ይሉና ቆየት ብለው እየሰጉ በኢትዮጵያም ሙስናን ለማጥፋት ብዙ አልተሰራም መስተካከል አለበት ይላሉ:: አቦይ አፋቸውን ሞልተው የኤፈርት ድርጅቶች ግን እስከ ቅርብ ግዜ ራሳቸው ነበሩ ዳይሬክተር:: የኤፈርት ድርጅቶች በዘመድ አዝማድ ተሳስረው ሲበዘብዟቸው አቦይ ፈላጭ ቆራጭ ነበሩ:: አሁን ራሳቸውን ወደ ደጅ አውጥተው ግን ነግረውናል::ታዲያ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ትግራይ እያለ ትግራይ በሙስና (ኪራይ ሰብሳቢነት) የተሻለች ነች ማለት ትክክል አይደለም:: ጠ/ ሚኒስትር እንደሚያውቁት ህወሃት በትጥቅ ትግል ወቅት የነበረው እምነት ለሁሉም መጥፎ ይሁን በጎ ህዝብ መስታወት ነው ከህዝብ የሚደበቅ ነገር የለም የሚል እምነት ነበረን:: በአሁኑ ግዜ ህዝብ የኛ መስታወት ነው የሚለው ቀርቶ በአሁኑ ግዜ ለህዝብ እኛ ነን መስታወትህ እየተባለ ነው:: ሃቁን ግን ህዝብ የማያውቀው ነገር የለም:: ስለዚህ ጠ/ ሚኒስትር ዋናው ነገር ግን በኢህአዴግ መንደር ሙስና መምታት ከተጀመረ ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጣት ያለውን ሰውነት ስለሚቆራርጥ አደገኛ ስለሆነ ጠ/ ሚኒስትሩም አይጨክኑም ሌሎችም ሃብት ስላካበቱ የመከላከል አቅማቸው ሃያል ስለሆነ ኪራይ ሰብሳቢዎች ተሸፋፍነውና ተቻችለው መኖር ነው የሚመርጡት::

<u>ወይን መፅሔት ቁ. 39 ገፅ 11</u>

በቅርብ ግዜ ተሻሽሎ የወጣ የከተማ መሬት አዋጅ መሰረት ያደረጓቸው ዋነኛው ጉዳይ ምንድን ናቸው? ከዚህ አዲስ አዋጅ የተያያዘ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰማሉ:: ለምሳሌ ህዝብ አልተወያየበትም በቅድሚያ መወያየት ነበረበት የሚል አስተያየት ይሰነዘራል:: ከነባር ይዞታ ባለንብረትነት በተዛመደ ስጋቶች የሚነሱ ስለሆነ በአጠቃላይ ስለ መሬት አዋጅ ህዝብ ሊረዳው ከሆነ ምን ማድረግ አለበት ይላሉ?

<u>ጠ/ ሚኒስትር</u>

ይህ አዋጅ ያስፈለገበት ምክንያት ሰፊ መሬት ይዘው ትንሽ በቆርቆሮ ቤት ሰርተው በመሸጥ ሃብታም ሊሆኑ የሚፈልጉ ሰዎች ነበሩ:: ውይይትም ማድረግ ተገቢ ነበር:: መሬት ይዞ ቤት ከሰራ የግሉ ቤት ናት መሬቱ ግን የመንግስት ነው:: ያ መሬት ሲሸጥ ገንዘብ ከጨመረም የሊዝ ገንዘብ የመንግስት ይሆናል ብለዋል:: መሬት እየሰበሰቡም ሃብታም መሆን ለሚፈልጉም ማገቻ ነው:: ለእነዚህ በመቅጣት የሊዝ ዋጋም ሊወርድ ይችላል:: መሬት ሁሉ በሊዝ ተመን መሆኑ ከዚያ ከሚመጣ ገንዘብ አድርገው ኮንደሚንየም በመስራት ድሃ ተጠቃሚ ይሆናል ይላሉ ጠ/ ሚኒስትር::

ጠ/ ሚኒስትር መጀመሪያ ወደ ትግል ስንወጣ ዋና መፈክራችን መሬት ላራሹ የፊውዳል ጭሰኝነትን በማባረር ድሃው ባለመሬት ሊሆን ነበር:: የደርግ መንግስት የህዝብ ሃብት ቤት ሲወርስም የህዝብ መሬትና ቤት የሚቀማ መንግስት እያልን እንደ መምቻ በትር በመጠቀም ህዝብን እየቀሰቀስን ወደ ትጥቅ ትግሉ እንዲተም አድርገናል::

ኋላም ጠ/ ሚኒስትር የራሻ፣ የአልባኒያ፣ የማኦ ኮሚኒስት አስተሳሰብ እየተጠናወተን እያለም መሬት የመንግስት ነው አላልም:: መሬት የመንግስትና የህዝብ የተባለውም በኋላ ነው:: በሌላ በኩል ህወሃት ኢህአዴግ መሬት የመሸጥ የመለወጥ ጉዳይ በኢህአዴግ መቃብር ብቻ ነው እያለ ቆይቶ ህወሃት ኢህአዴግ ክፍት ቦታ ከገጠር አርሶ አደር በጣም አነስተኛ ግምት እየተሰጠ መሬት በመሸጥ ሃብት አካብቷል:: ታድያ ኢህአዴግ አቋሙ ምንድን ነው? እነዚያ ሰፋፊ መሬት ይዘው እየቆራረጡ መሬትን የሚቸበችቡ ያሉት እኮ የህወሃት ኢህአዴግ ባለስልጣኖችና ከነሱ ጋር የጠለቀ ግንኙነት ያላቸው ናቸው:: በአዲስ አበባና በየክልሉ ያሉት ከፍተኛ መሪዎች እኮ ከሁለት በላይ ህንፃ አላቸው ያውም ምርጥ ምርጥ ቦታ::

እንደ እኔ እምነት አሁን ያለው የሊዝ ፖሊሲ ለድሆች የሚጠቅም ነው የሚለው ከማጭበርበር አልፎ ሌላ ትርጉም አልሰጠውም:: ድሃው ህብረተሰብ ኮንደሚንየም የሚሰጠው ከሆነ ዋጋውን ከየት አምጥቶ ይከፍለዋል:: እስካሁን በኮንደሚንየም የሚበዛው መካከለኛ ገቢ ያለው የመንግስት ሰራተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው ነጋዴ ነው:: አብዛኛው ህዝባችን ደግሞ የዕለት ጉርስ የሌለው ነው:: እንደ አብነት ለመጥቀስ ድሃ የሚባል ፍጡር በኮንደሚንየም አልገባም:: ስለዚህ ይህ አዋጅ የህዝባችንን ዜግነታዊ መብት የነጠቀ ህዝብ እንደ ህዝብ የህወሃት ኢ.ህአዴግ ተገዥ የሚያደርግና ለዚህ ፓርቲ ጭሰኛ እንዲሆን ያደረገ አዋጅ ነው:: ይህ አዋጅ በነፍስ ወከፍ ኢ.ትዮጵያዊ ዜጋ ሸብር ያስገባ ነው::

ሌላ ባለቤት መሬት ሊሸጥ ከሆነ ሻጩን ባለቤት ጣራና ግድግዳ ያንተ ሲል የመሬቱን ዋጋ መንግስት ከወሰደ ባለ ግድግዳው ምንም ሊያገኝ አይችልም:: ለምሳሌ መቀሌ ከተመሰረተች 100 ዓመት ሆኗታል:: መቶ ዓመታት ያደረገ ቤት ጣራና ግድግዳው አርጅቶ ቤቱ የተሰራበት ድንጋይና የበሰበሰ እንጨት ተሰብስቦ ዋጋ አያወጣም:: ይህ ቦታ ዋጋውን ከፍ ሊያደርገው የሚችለው መሬቱ ነው:: እንግዲህ የመሬቱን ዋጋ መንግስት ከወሰደው ከመቶ ዓመት በላይ የተቀመጡበት የልጅ ልጅ የት ይግባ:: ደርግ እንኳን ቤት ሲወርስ የምትኖርበት ቤት ይሰጥሃል የንግድ ቤት ከሆነ የማይከራይ አይወርስም:: አዲስ ቤት ሊሰራ የሚፈልግ ከ250 እስከ 500 ሜትር ካሬ ቤት ሰርቶ ይሸጥ ነበር:: የአሁኑ መንግስት ግን 80 ሚልዮን ህዝብን ባዶ ያደረገ ነው:: አሁን እኮ የከተማ መሬት ብቻ አይደለም የሚወርስ ያለው የገጠርም መሬት የመንግስትና የህዝብ በሚል ሽፋን የገበሬን የመሬት ባለቤትነት እየነጠቁት ናቸው:: ሊያወርስ አይችልም በዋስትናም አያሲዝም አያከራይምም ጨንቆታል:: በሌላ በኩል ብድርና ቁጠባ ተቋማት ገበሬዎች ገንዘብ ከተበደሩ እዳው ካልተከፈለ መሬቱ ይያዝና ለገበሬዎች በማከራየት እዳውን ያስመልሳል:: ታዲያ ይህ መሬት መሸጥ አይደለም ህወሃት ኢ.ህአዴግ ራሱ ሊፈፅመው ራሱ ያወጣውን ህግ ያፈርሳል:: ሌላ ሲቃወመው አሰራር ህግ ጣስክ ብሎ ይቀጣል:: እንደዚህ ዓይነት ተግባር እጅጉን መጥፎና የማንም ዜጋ ማንነትን የሚነጥቅ ነው:: ስለሆነ ይህ አሰራር ለኢ.ህአዴግ እድሜ ማሳጠርያ ነው:: ለኢ.ትዮጵያ ህዝብም አልተመቸም::

<u>ወይን መፅሔት ቁ. 39 ገፅ 13</u>

የህወሃት ዕቅዶች በተለይ ከ10 ዓመት የህወሃት ጉባኤ የተወሰኑ የሰላም የልማት የዲሞክራሲ ዕቅዶች የተደረሱ መደምደሚያዎች በእንዴት ያለ ደረጃ ላይ ይገኛሉ ይባላል?

<u>ጠ/ ሚ/ መለስ</u>

የህወሃት እንቅስቃሴ መልካም ነው:: በመልካም አስተዳደርም ጥሩ ደረጃ አለን:: የህወሃት ኢ.ህአዴግ ከፍተኛ አመራር በ4 ዙር ስልጠና ተሰጥቷል:: ለመካከለኛ አመራር ለማሰልጠንም ዝግጅት እየተደረገ ነው:: የሴቶች ተሳትፎም ወደ አመራር እየመጡ ነው:: የሴቶች ማህበር ከግዜ ወደ ግዜ እየጠነከሩ ይገኛሉ:: የባለሃብቶችና የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አደረጃጀት እየተሻሻለ ነው:: ህወሃት በሚባል ድርጅት በአሁኑ ግዜ ጥሩ ፖለቲካዊ ጤናማነት ይታያል ይላሉ?

ጠ/ ሚኒስትር ለድርጅታቸው እንደፈለጉ መጥፎ ወይም ጥሩ ብለው ሊገመግሙት ይችላሉ? ሃቁ ግን ህወሃት ኢ.ህአዴግ በአሁኑ ግዜ አገር እንዴት ይለማል ሳይሆን ያሉኝን ካድሬዎች እኔ በምፈልገው በማንቃት ስልጣኔን እንዴት ይራዘማል የሚል ነው:: ለዚሁ እንደማረጋገጫ ለ4 ዙር በሺ. የሚቆጠሩ የህወሃት አህአዴግና አጋር ድርጅቶች ለ2 ወር ወይ ከዚያ በላይ በመንግስት የስራ ግዜ በመንግስት አበል የአንድ ፓርቲ ካድሬዎች በስም ከፍተኛ አመራር ሽፋን ማሰልጠን በራሱ ህገወጥነት ነው:: ይህ እንዳይበቃው መካከለኛ ካድሬዎችም በመካከለኛ አመራር ስም አሁንም በመንግስት የስራ ጊዜና ገንዘብ በመቶ ሺዎች ለማስተማር በየክልሉ ዝግጅት እያደረገ ነው:: ታድያ

ይህ ፍትሃዊ ነው:: ከዚህ በላይ የሃገሪቱን ሃብት ማባከን አይሆንም:: ይህን የኢትዮጵያ ህዝብ ይፍረደው::

በሁሉ መስክ በገጠር በከተማ የሴቶች ማህበር ጠንካራ እንደሆነ ነው የሚነግሩን ያሉት:: የሴቶች መብት እየተከበረ ካለ ሴቶች ራሳቸው ይመስክሩ እንጂ በእኔ እምነት ሴቶች ምንም አይነት ነፃነት አላገኙም:: ሌላው ይቅርና ብረት ታጥቀው ደርግና ሌሎች ኃይሎችን ያሸነፉ ጀግና ሴቶች የፖለቲካ ልምድ ያላቸው በመቀሌ፣ በአድዋ፣ በኪሓ፣ በሽሬ፣ በአክሱም፣ በዓዲግራት እንዲሁም በአዲስ አበባ ምን ዓይነት የተበላሸ ኑሮ እንደሚኖሩ ህዝብ ያውቃል:: የገጠር ሴት ተገድዳ ገንዘብ በማውጣት የተደራጀች እንጂ በማህበር ተደራጅታ ያገኘችው ነገር የለም:: ምናልባት ግን ጠቅላይ ሚኒስትር ወደ እናንተ የተጠጉ የተመቻቸው ሴቶች እንደ መለኪያ ወስደው እንዳይሆን እንጂ እኛ የምናውቃቸው ሴቶች በኑሮዋቸውና በመብታቸው የተመኙትን መብት አላገኙም:: ያገኟት ጥቅም ዲግሪና ዲፕሎማ ይዘው ወደ ስደት ከመሰደድ ህሊናቸው በማይፈቅደው ስራ ተሰማርተው ነው የሚገኙት:: በዚህ አንድ ዓመት ወደ ስደት ለመሄድ ከመቀሌ ኢሚግሬሽን ፓስፖርት ያወጡ የቁጥር ብዛታቸውን ከመቀሌ ኢሚግሬሽን ይጠይቁ::

ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ባለሃብቶች እየተደራጁ ነው ብለውናል:: የትኞቹ ባለሃብቶች ናቸው የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ነጋዴዎች ናቸው:: ይኸውሎት አሁንም ወዳጅ ጠላት መሃል ሰፋሪ የሚለው አሰላለፍ አመጡት:: ከእንግዲህ የኢትዮጵያ ህዝብ ኮሚኒስት ስርዓት የሚሸከም ጫንቃ የለውም:: እኔ እምልዎ ስርዓትዎን ተመልሰው ይፈትሹ::

ሌላ በዚህ ፅሁፋቸው የልማት ሰራዊት የሚሉት አነጋገር አለ:: ለመሆኑ ይህች ሃገር ለ17 ዓመት ደርግን ለማስወገድ እንደዘመትነው የምትጓዘው ያ የራሱ ቦታና ጊዜ ነበረው:: ልማት ግን ሳይንስ ነው በሙያ መመራት አለበት:: በቀበሌ መሪዎችና ካድሬዎች አይመራም:: አሁን የልማት ሰራዊት የሚሉን በነዚህ በ4 ዙር ተምረው የመጡት ካድሬዎችና በሚቀጥለው የሚማሩ ካድሬዎች ነው የሚመሩት:: የእርሻ፣ ሳይንስ፣ የመአድን፣ የጤና፣ የትምህርት፣ ኢኮኖሚስት ተመራማሪውስ ምን ይስራ:: ካድሬ በየትኛው ሙያው ይምራው:: በእኔ እምነት የአፈርና የውሃ ጥበቃ በዘመቻ ሊሰራ ይችላል:: ያም ያለባለሙያ አመራር አይሆንም:: ስለሆነ ከፓርላማ እስከ ቀበሌ ያለው መዋቅር ልማታዊ ሰራዊት የምትል ቃል ልክ አሸባሪ የምትባል ስድብ ከፓርላማ እስከ ቀበሌ የተዘረጋችው ይህች ልማታዊ ሰራዊት የምትለው እስከ ቀበሌ ስትነገር ትርጉም አጣሁለት::

በማጠቃለል ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በወይን መፅሔት ቁ. 39 የሰጡን ማብራሪያ ከተጨባጭ መረጃ ያልተነሳ የተናገሩትና በመሬት ያለው ፍፁም የማይመሳሰል ነው:: ስለሆነም የፊልድ ዙረት ቢያደርጉ ሃቁን ያውቃሉ ለእርስዎም እንደ ተሃድሶ ይሆናልና መዋቅርዎን ይፈትሹ::

ሌላ የህወሃት ልሳኖች በተለይ ወይን ጋዜጣ፣ ወይን መፅሔትና ድምፅ ወያነ ትግራይ ህወሃት ትግል ከጀመረበት ጊዜ ቆየት ብለው በቅደም ተከተል የመጡ ነበሩ:: የነዚህ ልሳኖች ውጤት በትግሉ ወቅት ንቃት የሚሰጡ የሚያደራጁና የሚያስታጥቁ ነበሩ:: የትግራይን ህዝብ በአንድ ሰልፍ ወደ ትግል ተምሞ እንዲዘምት አድርገዋል:: ለደርግም በሚሰሩት ስራ ትጥቁን ያስፈቱት እነዚህ ነበሩ::

አሁን ግን ይዘውት የሚወጡት ቁምነገር በህዝብ ካሉት ሁኔታ ያላገናዘበ የህዝቡን ስሜትና ፍላጎት ጠምዝዘው የማይቀርቡ ይቅርና በትግል ግዜ የነበራቸው ተወዳጅነት ሊኖራቸው በአሁኑ ግዜ የሚያነባቸው የሚያደምጣቸው ቁጥሩ እጅጉን ጥቂት ነው::

በተለይ ድምፅ ወያነ ትግራይ ይዘት ያለው የዘቀጠ ፕሮፓጋንዳ አሳፋሪ ነው:: ይህን ልልበት የቻልኩት ከአሁን በፊት በእኔ የተፃፈ ጋህድ አንድ የሚል በህወሃትና ሻእቢያ የነበረው

ግንኙነት በጌታና ሎሌ የተመሰረተ ለሚለው በትግራይ ክልል በብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ በፀጋይ ሃዱሽ እየተዘጋጀ ድምፅ ወያነ ትግራይ ከሁለት ወር በላይ ፀረ—ጋህድ ጥሩንባውን ሲነፋ ተጠምዶ ከረመ::

አሁን ደግሞ ጋህድ ሁለት መፅሓፍን ለአቶ አስገደ ነጥሎ ለመምታት ለሳምንት ማስታወቂያ ሲናገር ሰንብቶ ከ21/6/2004 ዓ.ም ጀምሮ እየደሰኮረ ነው:: ይህ አሰራር ለድምፅ ወያነ ዝቅጠትና ውርደት ለጋህድ መፅሓፍቶችና ለአቶ አስገደ ክብር መስጠት ነው:: ስለሆነም እነዚህ የህወሃት ልሳኖች ወደ ግለሰቦች ወርደው ስም ማጥፋትና ህዝብን ማደናገር ቢታቀቡ መልካም ነው:: የሚመለከታችሁ የፕሬስ ሰዎችም ይህ ጉዳይ ከጠዋቱም ለሌሎች ፀሓፊዎች አደጋና ነፃነት የሚነጥቅ ስለሆነ ብትቃወሙት እላለሁ::

የህወሃት ልሳኖች የአገራችንን ህግ ተከትለው የሚሄዱ ቢሆን የፓርቲ ልሳን ሆነው ይቅርና ለመንግስታዊ ድርጅቶች ሆነ ለግል ድርጅቶች ማስታወቂያ ሊሰሩ አይችሉም:: ግብር የሚከፍሉ ነፃ ፕሬሶች ምን ይስሩ:: ለተወዳዳሪ ፓርቲዎችስ ለምን ይከለከላል:: ህግ ስለሆነ አያደርጉትም::

እስቲ ተመልከቱ ቁ. 39 ወይን መፅሔት የያዘውን 70 ገፅ እስፖንሰር ያደረጉት 63 የመንግስት 12 የኤፈርትና የጥረት 8 የግል ድርጅቶች በድምሩ 83 ድርጅቶች ስፖንሰር ሆነዋል:: ህዝቡ እንዲያውቃቸው ስፖንሰር ያደረጉት ድርጅቶች ከዚህ ዕሁፍ አያይዤዋለሁ:: ህዝብ ትዝብቱን ያሳርፍበት:: በቸር ያሰንብተን::

<u>የመንግስት ድርጅቶች</u>

1. መቐለ ዩኒቨርስቲ
2. ኢንስቲትዩት አመራር ስራ ትግራይ ክልል ትግራይ
3. ኤጀንሲ ማስፋፋት ህብረት ስራ ማህበር ልማትና ገበያ ክልል ትግራይ
4. ኮሌጅ ሳይንስ ጤና ዶክተር ተወልደ ለገሰ
5. መቐለ ኢንስቲትዩት ቴክኖሎጂ ቲሹ ካልቸር
6. ኢንተርፕራይዝድ ውሃ ስራ ክልል ትግራይ
7. ኢንተርፕራይዝድ ዲዛይንና ቁጥጥር ውሃ ስራ ትግራይ
8. የትግራይ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሃብት
9. የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር
10. የኣላጀ ወረዳ አስተዳደር
11. የትግራይ ክልል ፋይናንስና እቅድ ቢሮ
12. የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
13. የሰሃርቲ ሳምረ ወረዳ አስተዳደር
14. የትግራይ ክልል ጤና ቢሮ
15. የኢትዮጵያ አየር መንገድ
16. አግአዚ የፍትህ አካላት ማሰልጠኛ ማዕከል ውቅሮ
17. ዋተር ወርክስ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝስ
18. የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ
19. የኢትዮጵያ የውሃ ስራዎች ዲዛይንና ቁጥጥር
20. የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን
21. የኮረም ከተማ አስተዳደር
22. የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት
23. የኢትዮጵያ የቡና ተክል ልማት ድርጅት
24. የጋንታ አፈሹም ወረዳ አስተዳደር
25. የአዲ አህፈሮም ወረዳ አስተዳደር

26. የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር
27. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ
28. የትግራይ ክልል ምክር ቤት
29. የሽራሮ ወረዳ አስተዳደር
30. የአክሱም ከተማ አስተዳደር
31. የራያ ወረዳ አስተዳደር
32. የኢትዮጵያ ቴሌኮም
33. የናዕዴር ዓዴት ወረዳ አስተዳደር
34. የአዲግራት ከተማ አስተዳደር
35. የወልቃይት ወረዳ አስተዳደር
36. ኤጀንሲ ጥበቃ ስነ አካባቢ የመሬት አስተዳደርና የመሬት አጠቃቀም
37. የታህታይ ማይጨው ወረዳ አስተዳደር
38. የኦፍላ ወረዳ አስተዳደር
39. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን
40. የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ
41. የትግራይ ክልል ውሃ ሃብት ቢሮ
42. ህዝብና መንግስት ግንኙነት ቤት ላእላይ አድያቦ ወረዳ
43. የህንጣሎ ወረዳ አስተዳደር
44. የማይጨው ከተማ
45. ማይጨው ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ
46. የአላማጣ ከተማ አስተዳደር
47. የትግራይ ክልል ኤጀንሲ ፕሮሞሽን የእርሻ ምርት ግዥ
48. የኢትዮጵያ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
49. የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ክልል ትግራይ
50. የሽሬ ከተማ አስተዳደር
51. የመረብ ለኸ ወረዳ አስተዳደር
52. የእንዳ መኾኒ ወረዳ አስተዳደር
53. የኢትዮጵያ የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት
54. ኢትፍሩት
55. ወረዳ ፀገዴ አስተዳደር
56. ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ
57. የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ
58. ፋፋ የምግብ አክስዮን ማህበር
59. የባህርና የትራንዚት አገልግሎት ድርጅት
60. የደረቅ ወደብ አገልግሎት
61. ድሬዳዋ የንግድና ኢንዱስትሪ ቀልጣፋ አገልግሎት
62. የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ድርጅት
63. የሁመራ ሰቲትና የሁመራ ከተማ አስተዳደር

<u>የኤፈርት ድርጅቶች</u>

1. መስፍን ኢንጅነሪንግ ካምፓኒ
2. ሳባ እምነበረድ
3. መሶቦ የህንፃ መሳርያዎች ማምረቻ (ሲሚንቶ ፋብሪካ)
4. የትግራይ እርዳታ ማህበር (ሬስት)

5. ዳሸን ቢራ (ጥረት)
6. ደደቢት ኩእሶ (ደራ) ካምፓኒ
7. ዲማ ማር ፋብሪካ
8. ሜጋ ህትመት ኮርፖሬሽን
9. የባህርና ትራንዚት
10. ዕሰል ሓረስታት ፌዴሬሽን ግብይት ትግራይ
11. ኢዛና ኩባንያ ማዕድን ልማት
12. ትራንስ ኢትዮጵያ

<u>የግል ድርጅቶች</u>

1. ሸባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ
2. የኖክ ነዳጅ ማደያ ኖክ መቐለ
3. ደርባን ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ
4. ደስታ ማተሚያ ቤት መቐለ
5. ፎቶ ደስታ መቐለ
6. ቤን መስከረም ሆስፒታል መቐለ
7. ጎኪ ፕላስቲክ ንግድ ኢንዱስትሪ
8. ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሃገረስብከት ዓዲግራት

አስገዶ ገ/ ስላሴ ወ/ ሚካኤል ከመቐለ